MCPS ቅጽ 496-3
ዲሰምበር 2024
ከባለ 2 ገጾች 1ኛው

Summer RISE
Connecting Students to Careers

# Summer RISE 2025 Student Agreement
# ሠመር ራይዝ 2025 የተማሪ ስምምነት

Department of Partnerships
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
850 Hungerford Drive, Room 149, Rockville, Maryland 20850

## PARENT/GUARDIAN/ELIGIBLE STUDENT CONSENT የወላጅ/ሞግዚት/የብቁ ተማሪ ስምምነት

የሠመር ራይዝ 2025 ፕሮግራም የተነደፈው በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለሚማሩ ወጣት ጁንየሮች እና ሲንየሮች በ 2025 የሠመር ወቅት የሙያ ሥራ ትምህርት ልምድ እና እውቀት የሚገበዩበትን እድሎች ለማመቻቸት ነው። ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም ስመዘገብ፥ MCPS 11ኛ ክፍል ወይም 12ኛ ክፍል የተመዘገብኩ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጁንየር ወይም ሲንየር ተማሪ ስለሆንኩ 2025-2026 የትምህርት ዓመት የሠመር ፕሮግራም ብቁ መሆኔን አረጋግጣለሁ። ከወላጆቼ/ከአሳዳጊዬ ጋር ተስማምተን በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ለመሳተፍ ሙሉ ኃላፊነት እወስዳለሁ።

1. ከጁን 23, 2025 ጀምሮ እስከ ጁላይ 25, 2025 የሚካሄደው የሠመር ራይዝ መርሃ ግብር እስከ 5 ሳምንት ድረስ እንደሚካሄድ እና ቢያንስ 50 ሰአታት በተግባር መከታተል እንደሚኖርብኝ ተረድቻለሁ። በተመደብኩበት (የሙያ ልምድ ሰጪ) የቢዝነስ ተቋም፣ ድርጅት፣ ወይም ኤጀንሲ፣ "የሙያ ልምድ" ለማግኘት በሙያ ላይ የተመሰረተ በተግባር የመማር እድል የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊ በመሆን በቀን ከ 8 ሰአት ያልበለጠ እና በሳምንት ከ 40 ሰአት የማይበልጥ ጊዜ በሙያ ሥራ ልምምድ ቦታ እንደማሳልፍ ተረድቻለሁ። የሥራ ልምምዱ ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 7፡00 A.M. እስከ 6፡00 P.M. ሊካሄድ ይችላል። ከእነዚህ ሰአታት ውጭ ለመሳተፍ ከመረጥኩ፣ ከቀኑ 9፡00 P.M. በኋላ መስራት የማልችል በመሆኑ፣ ለእኔ የስራ ልምምድ እድል ለመስጠት የሚቀበለኝ ተቋም ለሠመር ራይዝ ማስተባበሪያ ቢሮ በቅድሚያ ሊገለጽለት ይገባል። የእኔ መርሃ ግብር ልምምዱን ከመጀመሬ አስቀድሞ በአስተናጋጁ ተቋም የሚወሰን ሲሆን ለእኔ ማረጋገጫ ይደርሰኛል። የሚጠበቀውን የተማሪ አበል ለማግኘት በሙያ ክህሎት እና በፋይናንስ ትምህርት አውደ ጥናት ላይ 50 ሰአት መሳተፍ እና ማጠናቀቅ ይጠበቅብኛል። ከሙያ ልምድ ሰጪው አካል የሚመለከተው የሥራ ባልደረባ ("Career Experience Host Designee(s)") የሠመር ራይዝ ፕሮግራሙ ሲጠናቀቅ ተቀባይነት ያለው 50-ሠዓት የሙያ ሥራ ልምምድ ማረጋገጫ ይሰጣል።
2. ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከመመዝገቤ በፊት፣ "Career Interest Profiler" እና "Career Cluster Finder" በ Naviance እና/ወይም RIASEC በምማርበት ኮሌጅ/የሙያ ትምህርት አስተባባሪ ድጋፍ መውሰድ እንደሚጠበቅብኝ ተረድቻለሁ። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ቡድንን በሙያ ልምዴ ለመርዳት ለትምህርት ቤታችን የመረጃ አስተባባሪ እና የሙያ አማካሪ (CCIC) አምስት ዋና ዋና ምርጫዎቼን ለይቼ ማሳወቅ ይኖርብኛል።
3. ሠመር ራይዝ ከመጀመሬ በፊት በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ እንደምችል የወላጅ/አሳዳጊ ስምምነት ማረጋገጫ መስጠት እና ቀጥታ በአካል ወይም ቨርቹወል በሙያዊ ክህሎት ስልጠና እና የፋይናንስ አውደ ጥናት ላይ መሳተፍ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ።አውደ ጥናቱ የሚካሄደው ከሚፈለገው የፕሮግራም ሰአታት በተጨማሪ ነው። የስልጠናው ዝርዝር በኢ-ሜይል እንደሚላክልኝ ተገልጾልኛል።
4. እኔ በአካል የሙያ ልምምድ ማድረግ ካለብኝ፥ የሙያ ልምምድ እስከምወስድበት ቦታ ድረስ የመጓጓዣ ኃላፊነቱ የራሴ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ። በሞንትጎመሪ ካውንቲ (5–18 እድሜ) ያላቸው ተማሪዎች በሙሉ "Youth Cruiser SmarTrip card" በመያዝ "Ride On"፣ "Ride On Flex" እና አንዳንድ ሜትሮባስ "Metrobus" መስመሮችን በነፃ ለመጠቀም ይችላሉ። ስማርትሪፕ ካርድ "SmarTrip cards" ማመልከቻ በትምህርት ቤታችን እና በሌሎችም ቦታዎች ይገኛል። ስለ "Youth Cruiser SmarTrip" ካርድ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የኮሌጅ/የሙያ ስራ መረጃ አስተባባሪዎን ያነጋግሩ እና/ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትራንስፖርት መምሪያ ድረ ገጽ www.montgomerycountymd.gov/DOT-Transit/kidsridefree/ ይጎብኙ።
5. የሙያ ልምምድ ምደባ የሚደረገው በእኔ የሙያ ፍላጎት፣ የመኖርያ አካባቢ፣ በአካል፣ እና/ወይም ቨርቹዋል ምርጫዬን መሠረት በማድረግ ስለሚሆን እንደመገኘቱ ሁኔታ የሚወሰን መሆኑን ተረድቻለሁ።
6. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያልሆነ የግል ኢሜይል አድራሻ መፍጠር እና ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም እና የስራ ልምምድ እንዳደርግ ለሚቀበለኝ አካል ማሳወቅ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ። የሠመር ራይዝ ፕሮግራምን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃዎች ወደዚህ ኢሜይል አድራሻ ይላካሉ፥ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያልሆነውን እና ከ MCPS የሚላኩልኝን ኢሜሎቼን በየእለቱ ማየት እንዳለብኝ ከሠመር ራይዝ ቢሮ ተገልጾልኛል።
7. የእኔን መርኃግብር በሚመለከት ከሙያ ልምምድ ሰጪ የሚመለከተው ሠራተኛ ወይም ተወካይ (my "Career Experience Host Designee(s)") ጋር በቀጥታ የመከታተልና የመተባበር ኃላፊነት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ።
8. በጥሩ ሁኔታ ለመከታተል፥ ጥሩ ስነምግባር፥ ትክክለኛነት፥ ሥነ ሥርዓት፥ በፍጥነት መሥራት፥ አስተዋይነት፥ ተገቢ አለባበስ፥ እና አግባብነት ባለው የቢዝነስ ስነ-ምግባር እና ቨርቹወል የምሳተፍ ከሆነ፣ ቪድኦ ላይ መሆን እንደሚጠበቅብኝ ተገንዝቤአለሁ/ተስማምቻለሁ። በእኔ የስራ ልምምድ ተቀባይ/ተወካይ ድርጅት አማካኝነት ሊፈቱ የማይችሉ ጉዳዮች ካጋጠሙኝ ወይም ስጋቶች ካሉኝ፣ የእኔን የሠመር ራይዝ አስተማሪ ወይም MCPS Summer RISE Program office summer-rise@ mcpsmd.org ወይም 240-740-5599 በመደወል ማግኘት እችላለሁ።
9. በአካል በመገኘት የስራ ልምምድ ላይ ለመሳተፍ ከመረጥኩ፣ የእኔ የሠመር ራይዝ አስተማሪ ተባባሪ/ረዳት ወይም የሠመር ራይዝ ሰራተኞች የእኔን የሥራ ልምምድ በርቀት የመቆጣጠር አማራጭ እንደሚኖራቸው ተረድቻለሁ።
10. እኔን የስራ ልምምድ እንዳደርግ የሚቀበለኝ ተቋም የማጣራት እና ክትባቶችን ጨምሮ ሌሎች ተጨማሪ መስፈርቶች ሊኖሩት እንደሚችል ተረድቻለሁ። ጁን 23 የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከሚጀመርበት ቀን በፊት ማንኛውንም ተጨማሪ የማጣራት መስፈርቶችን ለማሟላት ከእኔ የስራ ልምድ ተቀባይ ተቋም/ተወካይ ጋር በቀጥታ ክትትል ማድረግ እና መስራት የእኔ ሃላፊነት መሆኑን ተገልጾልኛል። የሥራ ሙያ ልምምድ የሚሰጠኝን ድርጅት/አስተናጋጅ መስፈርቶች ማሟላት ካልቻልኩ፣ ከተገኘ ሌላ እድል እስከሚሰጠኝ እጠብቃለሁ።
11. በአካል እየተገኘሁ በሰመር ራይዝ ፕሮግራም የሥራ ልምምድ ለማግኘት ከተሳተፍኩ እና ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዘ ማናቸውም አይነት ገደብ ቢኖር በራሴ ፍላጎትና በወላጅ/በአሳዳጊ ፍቃድ ስለምሳተፍ ገደቦቹን የማክበር ኃላፊነት እንዳለብኝ በመረዳት ተስማምቻለሁ። በተቻለ መጠን፣ የሙያ ልምድ ለመስጠት ተቀባይ/ተወካይ በሞንትጎመሪ ካውንቲ አስተዳደር እና በ MCPS የተቀመጡትን የኮቪድ-19 ፕሮቶኮሎች መከተል አለባቸው። ለኮቪድ-19 ለተጋለጠ(ች) ተማሪ MCPS ምንም አይነት ሃላፊነት እንደማይወስድ ግንዛቤ አግኝቻለሁ።

12. የሥራ ልምድ ለሚሰጠኝ ድርጅት/my Career Experience Host ተቀጣሪ አለመሆኔን ተረድቻለሁ።የሥራ ልምድ የሚሰጠኝ ድርጅት ከሠመር ራይዝ ተሳታፊዎች ወዲያውኑ የሚያገኘው ምንም አይነት ጥቅም አይኖርም፣ እናም አንዳንዴ ሥራቸው እንኳ ሊስተጓጎል ይችላል። እኔ የስራ ልምምድ እንዳገኝ የሚቀበለኝ ድርጅት ስራዎች ላይ በቀጥታ እንደማልሳተፍ ወይም በመደበኛነት ወይም በቀጣይነት ስራ እንደማልሰራ (ፋይል ማደራጀት፣ ሌላ የፅህፈት ስራ ወይም ደንበኞችን ማስተናገድ) በመሳሰሉት ስራዎች ላይ እንደማልሳተፍ ተረድቻለሁ። ለእኔ የሙያ ልምምድ የሚሰጠኝ የቢዝነስ ተቋም/የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች የሚመለከት መግለጫ ይሰጠኛል፥ የእኔን ሚና፥ ኃላፊነቶች፥ እና ለቢዝነሱ/ለድርጅቱ ማከናወን ያለብኝን ተግባሮች ያስተምሩኛል። ሥራ አስፈጻሚው(ዋ) ወይም ማኔጀር በሚሠራው ሥራ ዉጤታማ በሆነ መንገድ ለመከወን የሚጠቀምበትን ስልት፣ ጥራት፣ ክህሎት፣ እና እውቀትን በጥልቀት በመሻት እነዚህን ተግባራት እፈጽማለሁ። በበርካታ የሥራ ቅጥር አካባቢዎች መጠቀም የምችለዉን ሙያ ለመማር እድል ይኖረኛል።

13. ስለ እኔ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሞክሮ ቅድመ ዳሰሳ እና የፕሮግራም መጨረሻ የዳሰሳ ሪፖርት ለማቅረብ ተስማምቻለሁ።

14. የገንዘብ ድጋፍ/ፈንድ ከተገኘ፣ ለፕሮግራሙ የወጪ ማካካሻ አበል እንደሚሰጠኝ በመገንዘብ ተስማምቻለሁ። አበሉ የሚሰጠኝ ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ከጨረስኩ በኋላ ነው። የሠመር ራይዝ ፕሮግራምን እንደጨረስኩ MCPS ከወላጅ/ከአሳዳጊ ፍቃድ ከተሰጠ በኋላ የአበል ቼክ ለማዘጋጀት ፈንዱን ለሚያስተዳድረው ባንክ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስሜን ያስተላልፋል። የድጎማ ቼኩ ክፍያ የሚፈፀመው በቂ የገንዘብ ድጋፍ (ፈንድ) በማግኘት ላይ የተመሰረተ እና ዝቅተኛው 50-ሰአት መስፈርት መሟላቱን/መጠናቀቁን በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤት ከተረጋገጠ በኋላ ፕሮግራሙ እስኪጠናቀቅ ድረስ እንደማይከፈለኝ ተረድቻለሁ። ቼክ ለመውሰድ በጋራ የሚመች ጊዜ አስቀድሞ ቀጠሮ ማስያዝ ያስፈልጋል። የተማሪ ክፍያን ሂደት በተመለከተ የእኔን ሠመር ራይዝ አስተማሪ ወይም Summer RISE Program office በዚህ ኢሜል summer-rise@mcpsmd.org ማግኘት እችላለሁ፥ ወይም 240-740-5599 በመደወል ጥያቄዎቼን ማቅረብ እችላለሁ።

15. በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ መሣተፌ የሙያ ልምምድ ባደረኩበት ተቋም (my Career Experience Host) ሥራ የማያስጠኝ መሆኑን እና በሠራተኝነት ለመቀጠር መጠበቅ እንደሌለብኝ ተረድቻለሁ።

16. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም በምሳተፍበት ወቅት ቪዲዮ ለመቀረጽ፣ ፎቶግራፍ ለመነሳት፣ እና/ወይም ("ፎቶ እና ቪዲዮ ለመልቀቅ") ከወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድ ማግኘት እንደሚያስፈልገኝ ተረድቻለሁ። ምስሎቹ እና/ወይም ሪኮርዶቹ ስለ ሠመር ራይዝ ለማስተዋወቅ ተጨማሪ ፈቃድ ሳይጠየቅ ለተለያዩ ዓላማዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ተስማምቻለሁ። በእነዚህ አጠቃቀሞች ምክንያት ምንም ክፍያ እንደማይሰጠኝ እና ምስሎቹ፣ ቪድዮቹ፣ ሪኮርዶቹ፣ እንዲሁም ማናቸውም በዚህ የሚከናወኑ ሥራዎች ባለቤትነቱ የ MCPS መሆኑን እገነዘባለሁ። ወላጆቼ/አሳዳጊዬ ፎቶ እና ቪዲዮ ለመነሳት እና ለሚፈልገው አካል ለማስተላለፍ ባይፈቅዱልኝም በሠመር ራይዝ ፕሮግራም መሳተፍ እንደምችል ተረድቻለሁ።

17. MCPS ስለ እኔ የነፃ ወይም የቅናሽ ዋጋ ምግብ (FARMS) ሁኔታ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአጋርነት ማስተባበሪያ መምሪያ፣ የሠመር ራይዝ ፕሮግራምን ለሚመራው ቢሮ እንዲያቀርብ የወላጅ/አሳዳጊ ፍቃድ እንደሚያስፈልግ ተረድቻለሁ። Department of Partnerships/የትብብር ዲፓርትመንት ለተማሪ ድጋፍ እና አጠቃላይ ሪፖርት ለማቅረብ ዓላማ በመረጃነት ለመጠቀም የተማሪዎችን FARMS ሁኔታ መረጃ ማግኘት ይፈልጋል። ይህ የተማሪ መረጃ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአጋርነት ዲፓርትመንት ውጪ ለማንም ሰራተኛ አይሰጥም። በተጨማሪም ወላጆቼ/አሳዳጊዬ FAARMS ሁኔታዬን መረጃ ለማጋራት ፈቃደኛ ባይሆኑም እንኳ በሠመር ራይዝ ፕሮግራም መሳተፍ እንደሚቻል ተረድቻለሁ።

18. የእኔ የሥራ ልምምድ ተቀባይ/ተወካይ ድርጅት ስለ እኔ የሥራ ልምምድ ተሳትፎ ከ MCPS ጋር መረጃ እንደሚለዋወጡ ተረድቻለሁ። የእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ወይም ተወካይ የሆነ ተቋም የሠመር ራይዝ ተሳታፊዎችን የሚመለከት ምንም አይነት መረጃ ለሦስተኛ ወገን አያጋራም።

19. ይህን የስምምነት ውል፣ በስራ ልምድ አስተናጋጅ መሥሪያ ቤት የተቀመጡትን ደንቦች እና መመሪያዎች፣ ወይም ማንኛውም ሌላ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ህጎችን ማክበር ካልቻልኩ፣ ከሠመር ራይዝ ፕሮግራም መሠረዝ እና ድጎማውን ለመቀበል ብቁ እንደማልሆን ተረድቻለሁ።

20. በሙያ ልምምድ ላይ እያለሁ አሳሳቢ ነገር ካጋጠመኝ ወደ "my Summer RISE" አስተማሪ ወይም ወደ "Summer RISE Program office" በዚህ በይነመረብ summer-rise@mcpsmd.org ወይም 240-740-5599 በመደወል በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ አለብኝ።

ስለ "Summer RISE 2025 Student Agreement" ለማመልከት የተማሪ ስምምነት ቅጽ በመመዝገቢያ ቅጹ ላይ ባለዉ ቦታ ምልክት እንዲደረግ ይገለጻል፥ እናም ይህ በኤክትሮኒክስ የሚቀርበው ስምምነት እና የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ ከግል ፊርማ ጋር ተመሣሣይ እና እኩል ተቀባይነት ያለው መሆኑን እንደተገነዘብክ(ሽ) ይቆጠራል።